የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክ/መ/ቁ 286228

ልደታ ምድብ 9ኛ ገቢዎችና ጉምሩክ ወንጀል ችሎት ጥቅምት 10 ቀን /2014 ዓ.ም

ዳኛ- መሰለ ንጉሴ

ከሳሽ - የፌ/ጠ/ዐ/ህግ-

ተከሳሽ- አቶ ብርሀነ ግርማይ አበራ

መዝገቡ የተቀጠረው ለፍርድ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለፍርዱ መነሻ የሆነው ከሳሽ ዐ/ህግ በቀን 29/12/2012 ዓ.ም ዕፎ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ይዘቱም ተከሳሽ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 168/1 (በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 44(1) እንደተሻሻለው) እና የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 20(2)፣(3) እና (4) እንዲሁም መንገደኞች ወደ ኢትዮጲያ ይዘውት ስለሚገቡት ወይም ከኢትዮጲያ ይዘውት ስለሚወጡት የውጭ ምንዛሬና ብርን አስመልክቶ ብሄራዊ ባንክ መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ/ም ያወጣውን መመሪያ ቁጥር FXD/49/2017 አንቀፅ 4.1.ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በ12/09/2012 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት አካባቢ ሲሆን ከአሜሪካ በረራ በማድረግ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ተሸከርካሪ ማቆሚያ ሲደርስ በተደረገ ፍተሻ ገደብ የተደረገበትን 63900 የአሜሪካ ዶላር ወደ አገር ሲያስገባ ስለተያዘ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል የሚልነው ፡፡ ከክሱ ጋርም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ተጠቅሶ እና ተያይዞ ቀርቧል፡፡

የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ ክሱ በችሎት ተነቦ ተከሳሽ እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ አቅርቦ በብይን ታልፏል፡፡ በመቀጠል የእምነት ክህደት ቃሉን ተጠይቆ ወንጀሉን አልፈፀምኩም በማለቱ የዐ/ህግ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡

ም/ኢር አብርሀም ወርቅነህ እና አህመድ ይማም የተባሉ የዐ/ህግ ምስክሮች ከአሜሪካ በሚመጣ ፍላይት ዶላር ይዞ የሚመጣ ሰው አለ በሚል ጥቆማ ደርሷቸው እና ተነግሯቸው ተከሳሽን ከአየር መንገድ ሲወጣ ጀምረው ተከታተለው ሊወጣ ሲል መያዛቸውን እና ሲፈተሽ 63,900 ዶላር መገኘቱን መስክረዋል፡፡ ሰላማዊት ያይና የተባለች የዐ/ህግ ምስክር

ደግሞ መንገደኞችም ሆነ የአየር መንገዱ ሰራተኞች ዶላር ይዘው ሲመጡ በጉምሩክ በኩል ሲለሚያልፉ አስመዝግበው እንዲያልፉ እንደሚነግሯቸው እና ፎርምም እንደሚሰጧው መስክራለች፡፡

በሰነድ ማስረጃ ረገድ የተከሳሽ ፓስፖርት እና ቪዛ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኛ መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ፣ በእለቱ ተከሳሽ ከአሜሪካ የመጣ መሆኑ የተገለፀበት ሰነድ፣ ዶላሩ ባንክ የተቀመጠበት እና ስለ አሰራሩ የተፃፈ ማብራሪያ፣ ጉምሩክ ኮሚሽን ተከሳሽ ወደ አገር ሲገባ ምንም ዶላር እንዳላሳወቀ የገለፀበት ሰነዶች ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሽ በክሱ በዝርዝር በተጠቀሰው አግባብ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ 63,900 ዶላር ይዞ መግባቱን፣ ይህንን ዶላር ድክሌር ሳያደርግ ደብቆ ከኤርፖርት እና ጉምሩክ ፍተሻ ወጥቶ ሲሄድ መያዙን፣ የውጪ ምንዛሬ ይዘው የሚገቡ ሰዎች በጉምሩክ ዲክላራሲዎን ዲክሌር እንዲያደርጉ የሚነገር መሆኑን የዐ/ህግ ሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ የሚያስረዱ መሆኑን፣ ክስ የቀረበበት የህግ ድንጋጌ ማንም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የተከለከሉ፤ ገደብ የተደረገባቸው ወይም የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎችን ወደ ሀገር ካስገባ ፤ ከሀገር ካስወጣ ወይም ከሀገር ለማሰወጣት ወይም ለማስገባት ከሞከረ በወንጀል እንደሚያስጠይቅ የተደነገገ መሆኑን፣ እቃ ገንዘብን እንደሚጨምርም በአዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀፅ 2 /1/ ስር የተመለከተ መሆኑን፣ ሰዎች የውጪ ምንዛሬ የሚይዙበትን እና የሚጠቀሙበትን ገደብ ብሔራዊ ባንክ እንደሚያወጣ በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀፅ 20/2/ የተመለከተ መሆኑን እና ከ1000 ዶላር በላይ ወደ አገር ውስጥ ይዞ የሚገባ ሰው በጉምሩክ ዲክላራሲዮን ማስመዝገብ እንዳለበት ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር FXD/49/2017 አንቀፅ 4.1 ላይ የተቀመጠ መሆኑን፣ ተከሳሽም ይህ ስርዓት እና ገደብ እያለ በክሱ የተጠቀሰውን 63,900 የአሜሪካ ዶላር ዲክሌር ሳያደርግ ወደ አገር ውስጥ ይዞ ሲገባ መያዙ በዐ/ህግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በበቂ ሁኔታ መመረጋገጡን በመግለፅ ተከሳሽ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 168(1) (በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 44 /1/ እንደተሻሻለው) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በተከሰሰበት የኮንትሮባንድ ወንጀል እንዲከላከል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 142 /1/ መሰረት በቀን 02/10/2013 ዓ/ም ብይን ተሰጥቷል፡፡

ተከሳሽ ይከላከል ከተባለ በኋላ የሚያቀርበው መከላከያ ማስረጃ እንዳለ ተጠይቆ አለኝ በማለት በቀን 30/11/2013 ዓ/ም አንድ(1) መከላከያ ምስክር አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የተከሳሽነት ቃሉንም ሰጥቷል፡፡

ተከሳሽ በተከሳሽነት ቃሉ ሲሰጥ የአየር መንገድ የበረራ አስተናጋጅ ሰራተኛ መሆኑን በመግለፅ በቀን 12/09/2012 ዓ/ም ከአሜሪካን ሀገር ወደ ኢትዮጲያ ስራውን ጨርሶ እንደመጣ እና የጉምሩክ ቦታውን አልፎ እንደሄደ እና ከአሜሪካን ሀገር ኢትዮጲያ መሬት ሊገባበት በማሰብ ይዞት የመጣው ዶላር ይዞ እንደነበር እና እዛው ኤርፖርት ውስጥ ያለ ባንክ መንዝሮ ለመውጣት እና ወደ ቤቱ ለመሄድ ራይድ መኪና ተሳፍሮ እየሄደ እያለ የጥበቃዎቹን ቦታ ሳያልፍ የማያውቃቸው ሰዎች መጥተው መኪናውን ዳር አቁመው እንደተባለ እና ሻንጣውን መፈተሽ እንደጀመሩ ከዛም ገንዘቡን እንደሚፈልጉ ሲገባው በፖስታ ገንዘብ እንደያዘ እና ገንዘቡን ወደ ባንክ ለመመንዘር እየሄደ መሆኑን እንደነገራቸው፤ አየር መንገዱ ተርሚናል 2 ውስጥ ባንክ እንዳለ ነገር ግን የአየር መንገዱ ሰራተኞች በተርሚናል 1 እንደሚወጡ እና እዛ ለመመንዘር ስላልቻለ ሌላ አየር መንገድ ግቢ ውስጥ ያለ ንግድ ባንክ ለመመንዘር እየሄደ እንደነበር እንደነገራቸው፤ ከዛም አጅበውት ወደ ፌደራል ፖሊስ ዋና መስሪያ ቤት እንደወሰዱት እና ከውጪ ሀገር የመጣ በመሆኑ ማቆያ መግባት አለብህ ተብሎ ማቆያ እንደቆየ ከዛም ሲጨርስ ባምቢስ የሚገኘው ምርመራ ክፍል ወስደውት ቃል እንደሰጠ፤ አየር መንገዱ ውስጥ ለመንገደኛ አናውንስመንት እንደሚሰጥ እና እሱ የሚያውቀው የሚባለው ከሀገር ውስጥ ወደ ውጪ በሚመለስበት ጊዜ ችግር እንዳያጋጥሞ ገንዘብ ካሎት አስመዝግቡ የሚል እንደሆነ እና የዐ/ህግ ምስክር ያለችውን እሱ እንደማያውቅ ገልጿል።

የተከሳሽ መከላከያ ምስክር ክፍሉ ታረቀኝ የራይድ ሹፌር መሆኑን በመግለፅ ግንቦት 12/2012 ዓ/ም ቦሌ አየር መንገድ የአገር ውስጥ ተርሚናል ውስጥ ቆሞ ባለበት ወቅት ተከሳሽ እንደጠራውና ተሳፍሮ ገንዘብ ስለያዝኩ እና እዚህ ኤርፖርት ውስጥ ባንክ ገብቼ ለመመንዘር ስለማስቆምህ እና ከዛም ደግሞ የረር አለማየሁ ህንጻ ስለምንሄድ ሌላ ሰው አትጫን እንዳለው፤ ከዚያም እየተንቀሳቀሱ እያለ እና ከዋናው በር ሳይወጡ ሲቪል የለበሱ ሰዎች መኪናውን አስቁመው ከፈተሿቸው በኋላ ወደ ፌደራል ፖሊስ ይዘዋቸው እንደሄዱ መስክሯል።

የሰነድ ማስረጃን በተመለከተ ከጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ዕ/ቤት በቁጥር 01/አ60/1471 በቀን 27/07/2012 ዓ/ም የተጻፈ ደብዳቤ ከተከሳሽ የተገኘው 63,900 ዶላር የተወረሰ መሆኑን የሚገልፅ ደብደቤ አይይዘው አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ተከላክሏል? ወይስ አልተከላከለም? ጥፋተኛ ሊባል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል።

የተከሳሽ መከላከያ ምስክር ቃል በአጭሩ ተከሳሽ የራይድ ትራንስፖርት አገልግሎት ፈልጎ እንደደወለ እና ከቦሌ አየር መንገድ የአገር ውስጥ ተርሚናል ጋር ተከሳሽን እንዳገኘው እና ተከሳሽ ገንዘብ ስለያስኩ እና እዛው አየር መንገዱ ያለ ንግድ ባንክ ሄጀ ዶላር ስለምመነዝር ወደ ሌላ ቦታም ስለምንሄድ ሌላ ሰው አትጫን እንዳለው እና እሱን ይዞ ሊወጣ ሲል እንደተያዙ የሚገልፅ ነው። የዐ/ህግ ምስክሮች ደግሞ ተከሳሽ ከአሜሪካ በሚመጣ ፍላይት ዶላር ይዞ የሚመጣ ሰው አለ በሚል ጥቆማ ደርሷቸው እና ተነግሯቸው ተከሳሽን ከአየር መንገድ ሲወጣ ጀምረው ተከታተለው የጉምሩክ ስነ ስርዓት የሚፈፀምበትን ቦታ አልፎ መኪና ይዞ ወደ ውጪ ለመውጣት በአየር መንገዱ ግቢ ውስጥ እያለ መያዛቸውን እና በፍተሻም 63,900 ዶላር እንደተገኘ የሚያስረዳ ነው። የሰነድ ማስረጃውም ተከሳሽ የአየር መንገዱ ሰራተኛ እደሆነ እና በእለቱ ከአሜሪካ እንደመጣ፣ ዶላሩን ዲክሌር እንዳላደረገ የሚያስረዱ ናቸው።

የውጪ አገር ገንዘብ ወደ አገር ውስጥ ይዞ የሚገባ ሰው ገንዘቡን በጉምሩክ ዲክላራሲዎን ዲክሌር ማድረግ እንዳለበት ይህንን ሳይፈፅም ይዞ ከገባ መወንጀል እንደሚጠየቅ ከላይ ተጠቅሷል። ተከሳሽም 63,900 የአሜሪካ ዶላር የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በሚፈፀምበት ቦታ ዲክሌር ሳያደርግ አልፎ ወጥቶ ትራንስፖርት ይዞ በአየር መንገዱ ግቢ ውስጥ ቢሆንም ወደ ውጪ ሲወጣ መያዙን የዐ/ህግ ምስክሮች በሚገባ አስረድተዋል። ተከሳሽ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል እና የመላከያ ምስክሩ ቃልም ተከሳሽ የጉምሩክ ስነ ስርዓት የሚፈፀምበትን ቦታ አልፎ መውጣቱን የሚያሳይ ነው። ይህም የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት ከሚያጠናክር በቀር ተከሳሽ በተቀመጠው የጉምሩክ አፈፃፀም ስርዓት እና ቦታ ዲክሌር ለማድረግ ወይም የጉምሩክ ማስፈፀሚያ ቦታውን ሳያልፍ በሚገኝ ባንክ ለመመንዘር በሂደት ላይ የነበረ መሆኑን አያሳይም። ተከሳሽ ዶላሩን ሳይመነዝር የጉምሩክ መፈፀሚያ ቦታውን አልፎ ወጥቶ እያለ ግቢ ውስጥ ባለ ሌላ ባንክ ለመመንዘር በሂደት ላይ ነበርኩ የሚለው ተፈፅሞ የተጠናቀቀውን የወንጀል ድርጊት የሚመልሰው አይደለም። መከላከያ ማስረጃውም በተቀመጠው ስርዓት ዲክሌር ስለማድረጉ ወይም ድክሌር ለማድረግ በሂደት ላይ የነበረ ስለመሆኑ እንዲሁም የጉምሩክ ማስፈፀሚያ ቦታውን ሳያልፍ መመንዘር የማይችል የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ አይደለም።

ስለሆነም ተከሳሽ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 168(1) በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 44/1 እንደተሸሻለው የተመለከተውን በመተላለፍ የተከሰሰበትን የኮንትሮባንድ ወንጀል የፈፀመ ፋተኛ ነው ተብሎ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 149/1 መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

በመቀጠልም ፍርድ ቤቱ የቅጣት አስተያየት እንደሚከተለው ተቀብሏል፡፡

የዐ/ህግ የቅጣት አስተያየት፡-